
[redacted]

ኢየሱስ ባስተማራቸውና የሰማይን ምስጢራት ሁሉ በገለጠላቸው ሐዋርያት መሠረት እምነት የምትከተል ሐዋርያዊት ቤተክርስቲያን የምታምነው እንደሚከተለው ነው፡-




*ከመስቀል* ፡-

ውኃና ደም በዘላለም መንፈስ በክርስቶስ ኢየሱስ ስም ስንጠመቅ ተገኙ። ሦስቱም ለማዳን በአንድ ይስማማሉ። ፩ኛዮሐ. 5:6-8። ዕብ.9:14። ቁ.19:20። ሉቃስ 24:47። ። የሐዋ.4:12። ቲቶ 3:5-7 የሐዋ.10:43።

*1ኛጥያቄ*- የክርስርቲያን መሠረት ማነው?

__*መልስ*__ ፡- ክርስቶስ ራሱ ነው። ክርስቶስ ራሱም የመሠረታት ሃይማኖት አንዲት ቅድስት የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን ናት። ኤፌ.2:20። የሐዋ.2:38-42። ማቴ.16:18-19። 1ኛቆር. 3:1-11።

*2ኛጥያቄ*- ጴንጠቆስጤ ማለት ምን ማለት ነው? በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ይገኛል?

__*መልስ*__ ፡- በግዕዝ መጽሐፍ ቅዱስና በአሮጌው አማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ " በጴንጠቆስጤ ቀን" እያለ በሐዋ.2:1 ተጠቅሶአል። ትርጓሜውም መንፈስ ቅዱስ የሚወርድበን ቀን የሚገልጽ የመንፈስ ቀዱስ በዓል ወይም የነጻነት በዓል ማለት ነው። ዘሌ.23:4-16። ዘጸ.12፣ ። ፩ቆር 16:8።



*3ኛጥያቄ*- አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ አንድ አምላክ የሚሆንበት እንደምን ነው?

__*መልሱ*__- አብ መንፈስ ነው። መንፈስም አንድ ነው። የማይወሰን ጽንፍ የሌለው በሁሉ የሚገኝ ስፋቱ ርዝመቱ ይህ ነው የማይባል ነገር ግን በሥጋ ሊገለጥ ሲፈልግ በመንፈሱ አሠራር በድንግል ማርያም ማሕጸን ቃሉን ሥጋ አድርጎ በልጁ ውሕደት ራሱን ለዓለም የገለጸ በመሆኑ አንድ አምላክ ነው። የዳዊት መዝ.(139):7-11። ማቴ 1:20-23። ፩ኛጢሞ. 2:5፣ 3:16። ፪ቆሮ. 5:19፣ዮሐ 1:1-14። ቆላስይስ 2:9። ዕብ.1:3። ኢሳ.9:6።

*4ኛጥያቄ* መንፈስ ቅዱስ ከማን ይወጣል? ወይም ከማን ይሰርፃል?አካሉስ ምን አይነት ነው?

__*መልሱ*__- ከአብ ወይም ከኢየሱስ የሚወጣ መለኮታዊ ኃይል ወይም የእግዚአብሔርነቱ እስትንፋስ ነው። ኢዮብ.33:4። ሮሜ 8:9። ዘፍ.2:7። ዮሐ.20:22። መንፈስ ቅዱስ (የሐዋ.2:17) ከአብ ወይም ከኢየሱስ ውስጥ የሚወጣ መለኮታዊ ኃይል እንጂ ከግራ ወይም ከቀኝ ተነሥቶ የሚላላክ ሌላ አምላክ አይደለም። ቲቶ.3:6-7። ኢዮ.2:28። የሐዋ 2:1-17። እስትንፋስ በመስፈሪያ ስለማይለካ በቁመትም በወርድም ስለማይለካ እፍ እያለ የሚሰጠው የማይመጠን በየጊዜው ከእግዚአብሔር የሚፈስ የመለኮት እስትንፋስ ነው።

*5ኛጥያቄ*፦ የአብና የወልድ ልዩነት ምንድነው?

__*መልስ*__፦ አብ መንፈስ ነው። ዮሐ.4:23-24 እግዚአብሔር በሥጋ ተገለጠና ሰውና መንፈስ ሆነ። ኢሳ.9:6 ሰው ስለሆነ ልጅ ሆነ። ፍጹም አምላክ በመሆኑ የዘላለም አባት ነው።ስለዚህ አብና ወልድ አንድ ነው። ዮሐ.14:8-10። ፩ጢሞ.2:5። ፩ጢሞ.3:16። ዮሐ.1:1-14። ፪ኛቆሮ.5:19። ቆላ.2:9። ፩ኛጴጥ.3:18።ዮሐ 14:6። ዮሐ.2:19-22። ዕብ.10:6። ማቴ.1:20-23።



*6ኛ ጥያቄ*፦ ወልድ ያለው አብ አለውን?

__*መልስ*__፦ ወልድ ያለው አብ አለው። ወልድ የሌለው ግን አብ አኳን የለውም ምክንያቱም እግዚአብሔር በሥጋው ተገልጦአልና ዕብ.5:7-10። ፪ኛቆሮ.5:19። ቆላ.2:8-9። ፩ኛዮሐ.2:2-24። ዮሐ.14:7-11። ኢሳ.7:14። ኢሳ.9:6። ዮሐ.8:18-19። ዮሐ.10:30። ፩ኛጢሞ.3:16። ፩ኛጢሞ.1:15-17። 2:5-7። ሉቃ.10:22። ማቴ.11:27-29። ዕብ.10:5-7።

*7ኛ ጥያቄ*- አብ ወልድን መንፈስ ቅዱስን ትከዳለህን?

__*መልስ*__፦ አልከድም ፀትክክል አብ ወልድና መንፈስ ቅዱስ አንድ አካል እንደሆነ ከመጽሐፍ ቅዱስ በመገንዘብ አምናለሁ። ኢየሱስ የሚል ስም የመለኮት ስም እንደሆነና መለኮት በሥጋ ሲገለጽ እንደተጠራበትም አምናለሁ። መንፈስ ቅዱስ የአብ እስትንፋስ እንደሆነ እንጂ ከአብ ውጪ አካል እንደሌለው አምናለሁ። ዮሐ.4:24፤ የሐዋ.5:3-4። ኢዮብ. 32:8። 33:4። ዮሐ.5:43። ዮሐ.17:3-6። ማቴ.1:20-21። ፊሊጵ.2:9። ዮሐ.1:1-14። ኢሳ.9:7። ሚል.2:10።

*8ኛ ጥያቄ*፦ ሐዋርያት ለምን በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እንዲያጠምቁ ታዘው በኢየሱስ ስም አጠመቁ?

__*መልስ*__፦ ወልድ ያለው አብ አለው ወልድ የሌለው ግን አብ እንኳን የለውም ስለሚልና መዳንም የአብና የወልድ ስም በሆነው በኢየሱስ ብቻ እንደሆነ መልአኩ ገብርኤል ስለመሰከረና ክርስቶስም ኢየሱስ በቀባለው የአብ ስም እንደመጣ ስለመሰከረ በአዳኙ በኢየሱስ ስም አጠመቁ። የሐዋ.2:38። የሐዋ.4:12። የሐዋ.10:38፤ 48። ሉቃስ 24:47። ማቴ.1:21። ፊሊ.2:9። ፩ኛዮሐ.2:12። ቆላስይስ 3:17። ሚክ.5:2-4። ኤር.23:5-6። አብና ወልድ መንፈስ ቅዱስም የማዕረግ ስም

[illegible] የተጸውኦ ስም ስላለሆነ አላጠመቁበትም። ዐረግ ሰዎች ማጥመቅ አልተማሩምና።

*9ኛ ጥያቄ፦* ጥምቀት እንዴት ኃጢአትን ያስተሰርያል?

<u>*መልስ፦*</u> ሰው በኢየሱስ ክርስቶስ ስም የሚጠመቀው ፍጹም ጸጸትና ንስሃ ወደ ኢየሱስ ተመልሶ በእምነት ሲጠመቅ ከክርስቶስ የወጣው ውኃና ደም በስሙ አማካኝነት ኃጢአትን ስለሚደመስስ ጥምቀት የመዳን ጸጋ ያስገኛል። የሐዋ.2፡38። 10፡48። ሉቃስ.24፡47። ዮሐ.3፡5። ቆላስይስ.2፡11-14። ፩ኛዮሐ. 5፡6-8። የሐዋ.22፡16። ገላቲያ.3፡27። አማኝ ሲጠመቅ በደሉና ሞት የተፈረደበት አዳማዊ ስጋው ተገፎ በምትኩ ክርስቶስን በእምነት ለብሶ በአዲስ ሕይወት እንዲኖር ያበቃዋል።

*10ኛ ጥያቄ፦* የተጠመቀ ሰው ዳግም ሊጠመቅ ይችላልን?

<u>*መልስ፦*</u> ከሐዋርያት ሥርዓተ ጥምቀት ውጪ የሆነ ጥምቀት የተጠመቀ ሰው ካለ ጥመቀቱ ከንቱና የውኃ ዋና ይሆንበታል። በኃጢአቱም እንደታሠረ አለ። ማቴ.16፡18-19። ወይም እንደ መጥምቁ ዮሐንስ ትምቀት ይሆንበታልና የኤፌሶን ክርስቲያኖች ዳግም እንደተጠመቁ ሊጠመቅ ይገባዋል። ኃጢአቱን ተናዞ ለኃጢአቱ ሥርየትና ክርስቶስን ለመልበስ በኢየሱስ ስም በጥልቅ ውኃ ከተጠመቀ ግን መልካም አደረገ። ኤፌ.4፡5። የሐዋ.19፡1-6። ማር.16፡16። ያመነ የተጠመቀም ይድናል ያላመነ ግን ስለማይጠመቅ ይፈረድበታል። ማንኛውም ሰው ክርስቶስን የሚለብሰው በስሙ ሲጠመቅ ብቻ ነው። ገላ.3፡27። ገላ.1፡8-9። ቆላ.2፡11-14። ከክርስቶስ ጋር በጥምቀት ካልተቀበረና አሮጌውን አዳም አስጥግፎ አዲሱን አዳም ክርስቶስን ካልለበሰ እራቁቱን ነው። ሮሜ.6፡3-8። ቆላስይስ.2፡11-14። ገላ.3፡26-27። ፩ኛቆሮ.15፡39-50። ሮሜ.8፡1-3። ቁ.29-30። ራእይ 16፡15። ማቴ.22፡11-14።



*11ኛ ጥያቄ፦* ያለ ኢየሱስ ስም ጥምቀትና ያለ መንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ሰው ሊድን ይችላል? ዳግምስ ሊወለድ ይችላል?

<u>*መልስ፦*</u> ሊድን አይችልም። ሰው ከውኃና ከመንፈስ ካልተወለደ በቀር መንግስተ ሰማያት ለመውረስ ፍጹም አይችልም ሲል ኢየሱስ አስረግጠ አውጇል። ዮሐ.3፡5። ኤፌ.1፡13-14። ፩ኛቆሮ.12፡13። 6፡11። ፩ኛቆሮ.19፡20። የሐዋ.2፡1-4። 38። ቲቶ 3፡5-7። የሐዋ 10፡43-48። የሐዋ.19፡1-6። ማቴ.3፡11። ማር.9፡49። ሉቃስ 12፡49። ሉቃስ 11፡13።

*12ኛ ጥያቄ፦* ሰው ከውኃና ከመንፈስ ካልተወለደ የማይድን ከሆነ ከጌታ ጋር የተሰቀለው ወንበዴ ያለ ጥምቀት ለምን ዳነ?

<u>*መልስ፦*</u> ቤተ ክርስቲያን ከመጀመሯ በፊት ከአዳም ጀምሮ እስከ ትንሳኤው ቀን ድረስ የነበሩት ሰዎች በሕግና በተስፋ እንዳደኑ እንጂ በዳግም ልደት ጥምቀት እንዳልዳኑ መጻሕፍት ይመሰክራሉ። ፩ኛጴጥ.3፡18-19። 4፡6። ከጌታ ትንሳኤ በኋላ ከጴንጠቆስጤ ቀን ጀምሮ ግን ከጌታ ጋር መቀበርና መነሣትን ለማረጋገጥ በጥልቅ ውኃ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ለኃጢዓት ሥርየት ተጠምቀው በኪዳኑ ደም ታጥበው በመንፈስ ቅዱስ የታተሙ የተቀደሱ ምእመናን ይሆናሉ ነው። ከዚያ በፊት ግን ክርስቲያን የተባለ የለም። ከጴንጠቆስጤ ቀን ጀምሮ በሐዋርያት ትምህርት የተፈታ ይሆናል እንጂ ከስቅለትና ከትንሳኤ በፊት እንደነበረ ሥርዓት ቢሄድ ሊድን አይችልም። በሐዋርያት ትምህርት ያልተፈታ ግን በሰማያት የታሠረ ይሆናል። ማቴ 16፡18-19። የሐዋ.2፡38። ገላቲያ 1፡8-9። ገላቲያ 3፡27። ፩ኛቆሮ.3፡1-11። ኤፌ.2፡20-22። ዕብ.9፡19-20። የሐዋ.22፡16።

*13ኛ ጠያቄ፦* በዘፍ.1፡26 እግዚአብሔር እንፍጠር ማለት ሦስት አማልክት ወይም ሦስት ፈጣሪዎች አሉ ማለቱ ነው?

<u>*መልስ፦*</u> በዘፍ.1፡26-27 እግዚአብሔርም አለ ብሎ ይጀምራል ቀጥሎ እንፍጠር ይልና በነጠላ ቁጥር



"በመልኩ" በማለት አንድ አካል አንድ አምላክ መሆኑን ያረጋግጣል "እንፍጠር" ማለቱ ደግሞ እግዚአብሔር ከገዛ ፈቃዱ ጋር እየተማከረ ይፈጥር እንደነበረ መጽሐፍ ቅዱስ በኤፌ.1፡11 እና በኢሳ.44፡24 ያረጋግጣል። እግዚአብሔርን የሚያማክር ሌላ አማካሪ ወይም ረዳት እንዳልነበረው ራሱ አረጋግጦአልና። ዘፍ.1፡26-27። ሁሉን ነገር ብቻውን ለመፍጠሩ ከዚህ በታች ያሉትን ማስረጃዎች በማስተዋል ተመልከት። ኢሳ. 40፡12-15። ኢሳ.40፡28። ፩ኛሳሙ. 2፡3። ሚል. 2፡10። ኢዮብ 33፡4። ኢሳ. 44፡8። ይሁዳ 1፡4-5። ዮሐ. 1፡1። ኢሳ 43፡10፣ 13። ፪ሳሙ 7፡22። ዘፍ.1፡1፣ 1፡27። 2፡7 እግዚአብሔር በአካልም በመለኮትም አንድ ብቻ ነው። ዘዳ.6፡4። 32፡39-41። ዮሐ.3፡13። ዮሐ.17፡3። ዮሐ.5፡20።

*14ኛ ጥያቄ፦*እግዚአብሔር መንፈስ፣መንፈስ ቅዱስም መንፈስ ከሆነ ሁለት መንፈሶች አሉ ማለት ነው?

<u>*መልስ፦*</u> መጽሐፍ ቅዱስ "መንፈስም አንድ ነው።" ስለሚል እግዚአብሔር መንፈስ ነው። የሚሰግዱ ለትም በመንፈስና በእውነት ሊሰግዱለት ያስፈልጋ ቸዋል። መጽሐፍ ቅዱስ በእውነትና በመንፈስ ሆነን ለአንዱ መንፈስ መስገድ እንዳለብን ያመለክታል። ፩ኛቆሮ 12፡3-4። ዮሐ.4፡24። በኤፌ.4፡4-6 አንድ አካል አንድ መንፈስ አለ ይላል። የእግዚአብሔር መንፈስ ማለት የእግዚአብሔርን ሕይወት የእግዚአብሔርም መለኮታዊ እስትንፋስ የሚገልጥ እንጂ ከእርሱ ልዩ የሆነ መንፈስ አለ ማለት አይደለም።

*15ኛ ጥያቄ፦* አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ በቅርጽ ወይም በሥዕል ሦስት ሰዎች አስመስለው የቀረጹዋቸው በሰማይ እንደዚያው በሦስት አካል ይኖራሉ ብለው ስለሚያምኑ ነው?

<u>*መልስ፦*</u> የሥላሴ አማኞች በአገላለጽና በእምነት ይለያያሉ። አንዳንዶቹ ዘጠኝ መለኮትም እስከማለት የሚደርሱ አሉ። ቤንሂን የተባለውም የታወቀ የካርዝማቲክ ሰባኪ ይህን ያመለክታል። አንዳንዶቹም በሦስት አካላትና በሦስት መለኮት

በመነጣጠል የሚያምኑ ስለሆኑ የትሪቴይስቲክ ባሕሪይ ስላለባቸው ሦስት ሰዎች መሳይ እግዚአብሔሮች አሉ ብለው ስለሚያምኑም ሦስት ሰዎችን አስመስለው በመሳል ስዕላቸውን ያስተዋውቃሉ ይሰግዱላቸውማል። ሌሎቹ የሥላሴ አማኞች ደግሞ አንድ አምላክ ይሉና ነገር ግን አብ አምላክ ወልድ አምላክ መንፈስ ቅዱስም አምላክ በአካል ሦስት በስም ሦስት በግብር ሦስት በመለኮት አንድ በማለት ለሰው ግራ የሚያጋባ የመለኮትና የአካል አንድነትና ሦስትነት ይገልጻሉ። ምን ማለታችሁ ነው? ተብለው ሲጠየቁ ምስጢር ነው ዝም ብለህ እመን ይሉናል። መጽሐፍ ቅዱስ ግን እግዚአብሔር በአካልም ሆነ በመለኮት ግራ በማያጋባ ሁኔታ አንድነቱን ይገልጣል። ሮሜ.1፥20-25። ዮሐ.1፥1-14። ፩ጢሞ 3፥16። ይሁዳ ቁ. 3-4። ቁ.25። ኢሳ.9፥6። 44፥6-8። ቁ.24። ራእይ 4፥2። የኦክስፎርድ ዲክሺነሪ ኦፍ ክርስቺያን ቸርች "የስላሴ አማኞች በሐሳባቸው እወነተኛ በአገላለጻቸው ግን የሦስት አማላክት አማኞች ናቸው" ሲል ያጋልጣቸዋል። ገጽ 1396 2[nd] edition by F.L.Cross.

*16ኛ ጥያቄ፡-* የሥላሴ አማኞች ሥላሴን በእንቁላል ይመስሉታል። እንቁላል ሦስት አካል አላት ወይ?

__መልስ፡-__ እንቁላል አንድ እንጂ ሦስት አካል የላትም እግዚአብሔርም ሦስት መስሎ ይታያቸው እንጂ እስትንፋሱን ቃሉንና ልቡን አወላልቀው በሦስት ቢከፍሉት ሙሉ አምላክ ሊሆንላቸው አይችልም። ይህ በእግዚአብሔር መጫወት ይባላል። ትልቅ ድፍረትም ነው። ኃጢአትምነው። እኔ እግዚአብሔር አልለወጥም ይላልና። ሚል.3፥6 "አሁንም እኔ ብቻዬን እኔ እንደሆንሁ ከእኔም በቀር አምላክ እንደሌለ እዩ፤ እኔ እገድላለሁ አድንማለሁ። እኔ እመታለሁ እፈውስማለሁ ከእጄም የሚያድን የለም" ይላል። ዘዳ.32፥39። እግዚአብሔርን እናብዛ ብለው ለሚያስቡ በኢሳ. 11፥ መንፈሶች ዘጠኙ ከተቆጠሩና እንዲሁም መጽሐፍ ቅዱስ በተጠቀሱት መንፈሱ፣ ታሌ፣ከንዴ፣ጽድቁ፣ ማዳኑ፣ ቸርነቱ፣ ፍርዱ፣ ሕጉ (ኢሳ.51፥4-17። 56፥1። መዝ.90፥17። መዝ.35፥5-



6) ክበሬ ድምጼ ዘፍ.3፥8። እስትንፋሴ፣ ልጄ ነፍሴ፣ ልቤ፣ ደሜ፣ ሥጋዬ፣ እጄ፣ ቀኝ ስለሚል መዝ.98፥1። መዝ.89፥13። ኢዮብ. 32፥8። ዘፍ.2፥7። እነዚህ ሁሉና ሌሎችም እግዚአብሔር የጠቀሳቸው የባሕሪይው ክፍሎች በሙሉ በአካል መልክ እየቀረጹ መልክ ከሰጡአቸው አማልክትን መፍጠር ይቻላል እንደማለት ይቆጠራልና እንጠንቀቅ። እግዚአብሔር አንድ ብቻ ነው!

*17ኛ ጥያቄ፡-* ኢየሱስ በአብ ቀኝ ተቀመጠ ማለት ምን ማለት ነው?

__መልስ፡-__ አብ ቀኝና ግራ የለውም፤ሁሉ በሁሉ የሚገኝ መንፈስ ነው። በአብ ቀኝ ተቀመጠ ማለት ግን የአብን ኃይልና ሥልጣን ወረሰ ወይም መለኮትን ለበሰ ከስጋ ድካም ተለየ የአብ ቀኝ ወይም ክንድ ሆነ ማለት ነው። የአብ ኃይልና ጥበብ ኢየሱስ እንደሆነ ተጽፎአል። ፩ኛ ቆር. 1፥24። መዝ.98፥1። ኢሳ.51፥5። 53፥1። 59፥16-17። ሉቃስ. 22፥69። ማቴ.26፥64። ማቴ.28፥18። ዮሐ.16፥24። ም.15፥16። መዝ.89፥13። የእግዚአብሔር ኃይል በኢየሱስ ስም ውስጥ ነው። የእግዚአብሔር ኃይል በሥጋውና በደሙ ይሠራል። ዮሐ.6፥35-59። ራእይ.11፥15-18። 12፥10-12።

*18ኛ ጥያቄ፡-* መንግሥቱን ለአባቱ አሳልፎ ይሰጣል ልጁ ራሱ ደግሞ ሁሉን ላስገዛለት ይገዛል ሲል ወልድ ፍጡር ነውና ፍጡር ለፈጣሪ ይገዛል ማለት ነው? ፩ኛ ቆሮ 15፥20-28።

__መልስ፡-__ ቃል ስጋ ሆነ ይላል።ቃልም እግዚአብሔር ነው። ዮሐ.1፥1-14። እግዚአብሔር በስጋ ተገለጠ ይላል። ፩ኛ ጢሞ.3፥16። የመስቀል ቃል ኪዳን እስከ ምጽአት ቀን ብቻ ነው። ከዚያ በኋላ ግን ወንጌል ማለት የክርስቶስ መስቀል አይሰበክም። እግዚአብሔር በሥጋ ተገልጦ የሚሠራውን ሥራ ይፈጽማል። ከዚያ በኋላ እግዚአብሔር አንድ ስሙም አንድ ይሆናል። ዘካ.14፥9። እግዚአብሔር በሥጋው በኩል ሲሰራው የነበረውን ሥራ ከፈጸመ በኋላ ይህንን ተግንዞ ያልተቀበለ በልጁ (በሥጋው) መገለጡን ያላመነ በልጁ ሥልጣን



ይፈረድበታል። ሥጋውም በመለኮት መለኮትም በሥጋው እንደሆነ ይኖራል። በመስቀሉ ቃል የዳን ግን ሁላችን በሥጋው (በልጁ) ሲገለጥ የነበረውን የማይታይ መለኮታዊ ምስጢርን ፊት ለፊት እንመለከተዋለን። ለዘላለም ከእርሱ ጋር እርሱን መስለን እንኖራለን። ራእይ 1፥8። ሮሜ.9፥5። ቲቶ.2፥13። ዘካ.14፥5-9። ቆላስይስ 1፥15-21። ኤፌ.1፥4-10።ቁ.18፥23። ቆላስይስ.2፥8-10። ዮሐ.6፥3። ቁ.60። ፪ቆር.3፥17። 5፥16። ፩ኛ ዮሐ.3፥1-3። ፊል.3፥20-21።

*19ኛ ጥያቄ፡-* አብ በልጁ (በስጋው) ውስጥ የተዋሐደ(የተባበረ) ከሆነ ወልድ ወደ ማን ይጮህና ይጸለይ ነበር?

__መልስ፡-__ ወልድ ፍጹም አምላክና ፍጹም ሰው ነው። ፍጹም ሰው ስለሆነ ከመለኮት ጋር ሊያስታርቀን የምልጃ ጩኸት ይጮሃል፤ ያለቅሳል፤ ይራባል፤ ይጠማል፤ ይደክማል፤ ይጸልያል ስለ ሰዎች ለሁሉም ይማልዳል፤ እግዚአብሔርም በልጁ በክርስቶስ (በስጋው) ሆኖ ዓለምን ከራሱ ጋር የስታርቅ ነበርና ይላል። አብ መንፈስ ነው ሥጋና አጥንት የለውም። ከዘላለም ዘመን ያዘጋጀልንን መዳን ይሰጠን ዘንድ ሥጋን አዘጋጀ፤ ከሥጋውም ጋር ተዋሐደ። ዕብ.10፥6። ፪ኛ ቆር. 5፥19። ዮሐ. 6፥57። ም.14፥8። ም.4፥24። ቆላስይስ.2፥9። ኢሳ.9፥6። ማቴ.1፥23። ፩ኛ ጢሞ.1፥15-17። 3፥16። ሮሜ.9፥5። ዕብ.5፥7-11። ሉቃስ. 24፥39። በሥጋው ሞተ በመንፈስ ግን ሕያው ሆነ ። ፩ኛ ጴጥ.3፥18። ሰው ስለሆነ ሞተ አምላክ ስለሆነ በገዛ ሥልጣኑ ተነሳ። ዮሐ.2፥12። ወይም አብ ወልድን ወይም መንፈስ ሥጋውን አስነሣ። የሐዋ. 2፥24።

*20ኛ ጥያቄ፡-* በ፩ኛ ተሰ.5፥23 ላይ "__መንፈሳችሁም ነፍሳችሁም ሥጋችሁም__ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመጣ ጊዜ ያለነቀፋ ፈጽመው ይጠበቁ" ማለቱ ሰው ሦስት አካላት ኖሬውት ሦስቱም በየግላቸው ለፍርድ ይቀርባሉ ማለቱ ነውን?

__መልስ፡-__ የእግዚአብሔር ቃል ሰው የማይሞትና የሚሞት ተፈጥሮ በአካሉ እንዳለው ያረጋግጣል።

ቀዝቃዛ ሰው ከጭቃና ከመንፈስ እንደተፈጠረ ያረጋግጥልናል። ኢዮብ.32፥8 በሰው ውስጥ መንፈስ ማለትም የማይሞት ሕያው ነፍስ እንዳለው ያረጋግጣል። በ፪ኛ ቆር.4፥16 ደግሞ " የውጭው ሰውነታችን (ሥጋችን) ቢጠፋ እንኳ የውስጡ ሰውነታችን (ነፍሳችን) ዕለት እለት ይታደሳል" በማለት ሰው በአንዱ አካሉ መንፈስ ነፍስና ሥጋ እንዳለው እንደ ሦስት አካላት በሚመስል አነጋገር ቢነግርላቸውም ሰው ሦስት አካል መሆን እንደማይችል ሦስት ሆነውም በየግላቸው ወደ ፍርድ እንደማይቀርቡ እርግጠኞች ነን። ሰው በሥጋ ሲሞት ግን ነፍሱ ማለትም መንፈሱ ወደ ገነት ትሄድና አፈር ግን ፈርሶ (በስብሶ ) ይቀራል። ለፍርድ ሲነሳ ግን በአዲስ መልክ በአካል ሙላት ተነስቶ ለፍርድ እንደሚቀርብ ቃሉ ያረጋግጣል። ፩ኛ ቆር.15። የሐዋ.7፥59። ያዕ.2፥26። ማቴ.10፥28። ራእይ 20፥4። መክብብ.12፥7።

*21ኛ ጥያቄ፦* በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ለኃጢአታቸው ሥርየት ሳይጠመቁ አጋንንትን የሚያስወጡ፤ ትንቢት የሚናገሩ ታላላቅ ሰባኪዎች አልዳኑም ማለት ነው?

<u>*መልስ፦*</u> ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለጴጥሮስ በሰጠው ሥልጣን መሠረት በሐዋ.ሥራ.2፥38 ጴጥሮስ በተናገረው ቃል ያልተፈቱ በሰማያት የታሠሩ ናቸው። ማቴ.16፥18-19። የሐዋ.2፥38-42። መርምረው፤ አትለፈው! ማስጠንቀቂያ።

ጌታ ሆይ፤ጌታ ሆይ በስምህ ትንቢት አልተናገርንምን? በስምህስ ብዙ ተአምራት አላደረግንምን? ይሉኛል! የዚያን ጊዜ ከቶ አላውቃችሁም እናንተ አመጸኞች ከእኔ ራቁ ብዬ እመሰክርባቸዋለሁ ይላል። በማቴ.7፥22-23። እና በማቴ.16፥18-19 መሠረት ፈዋሾች ፈዋሽነታቸው ለደህንነታቸው ዋስትና ሊሆናቸው አይችልም። ጌታ ኢየሱስ የመፍታትና የማሠር ሥልጣን ለጴጥሮስ ስለሰጠው ለጴጥሮስ በተሰጡት ሦስት መክፈቻዎች በሐዋ.ሥራ 2፥38 መሠረት ካልተፈታህ በቀር በሰማይ ቦታ የለህም ። ጌታ ምጥቶ ግራና ቀኝ በሚከፍልበት ጊዜ እንዳታፍር የጴጥሮስን አዋጅ ተቀበል። ፪ኛ ተሰ.1፥8-10።



*22ኛ ጥያቄ፦ ጸጋ ማለት ምን ማለት ነው?*

<u>*መልስ፦*</u> ጸጋ ማለት ከእግዚአብሔር እንዲያው በነፃ ያለ ሥራ፤ያለ ድካም፤ያለ ዋጋ የተሰጠ የነፃ ስጦታ ማለት ነው። ኤፌ.2፥1-20

*23ኛ ጥያቄ፦ በጸጋ የተገኙ ስጦታዎች ምንና ምን ናቸው?*

<u>*መልስ፦*</u> የመስቀል ስጦታዎች ናቸው።

ሀ/ ከአባታችንና ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ አካል የወጡ ውኃውና ደም።
ዮሐ.19፥34። ዮሐ.6፥50-63። ፩ኛዮሐ.5፥6-8። ዕብ.9፥14 ቁ. 19-20። የሐዋ.20፥28።

ለ/ የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት። ማቴ.3፥11። ሉቃስ.12፥49። ሉቃስ.11፥13። ቲቶ.2፥5-7። ኤፌ.1፥13-14። የሐዋ.2፥17-18።

ሐ/ የመለኮት ስም " ኢየሱስ ክርስቶስ" ራሱ ጸጋ ነው፤ ስሙ መድኃኒት
ነውና። ማቴ.1፥20-23። ኢየሱስ ማለት፦(ደምና ውኃ መንፈስ ያለበት
መድኃኒት) ማለት ነው። ፪ኛቆሮ.3፥3-17። ፩ኛዮሐ..2፥12። ፩ኛዮሐ.5፥13።ማቴ.3፥11። ዮሐ.2፥12። ዮሐ.1፥33። እነዚህ ጸጋዎች ለደኅንነት በአንድ ይሠራሉ አይለያዩም።

መ/ ጥምቀት ጸጋ ነው። በጸጋ ድነናል ማለት ኃጢአታችንን እየተናዘዝን
(ምሳ.28፥13) ሕይወትን በሚሰጥ በአምላካችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም
ለኃጢአታችን ሥርየት ስንጠመቅ በዘላለም መንፈስ የፈሰሰው ደሙና ውኃው በጥምቀት በአንድነት በእምነት ብንወስድ ያድኑናል ማለት ነው።

ከዚያም በመንፈስ ቅዱስን መሞላት አለብን። ፩ኛዮሐ.5፥6-8። ዕብ.9፥14። ቁ.19-20። የሐዋ.2፥38። የሐዋ.10፥43-48። ዮሐ.3፥5።



ማቴ3፥5-11። ጥምቀት ራሱ የደህንነትን ጸጋ የሚያስጥ ስለሆነ ጸጋ እንጂ ሥራ አይደለም። እምነትና ሥራም ከተለያዩ ከንቱ ናቸው። ያዕ.2፥18-26።

አስተውልና የቀደመችውን መንገድ ያዝ ኤር.6፥16-21።

ዛሬ ከነጴጥሮስ ጋር በጌታ ቤት መገኘትንም ምረጥ። በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ለኃጢአትህ ሥርየት ተጠምቀህ ጸጋውን ተቀበል። የመንፈስ ቅዱስ ስጦታንም ተቀዳጅ። ለነፍስህም እረፍትን፤ ሠላምንና ፍቅርንም ታገኛለህ። በእግሮችህ ለመቆም የምትችለውና ከጥርጥር ነፃ የምትሆነው ከዚያ በኋላ ነው። ለምን ትዘገያለህ? የሐዋ.ሥራ.22፥16። እውነትን ብታውቅ እውነት አርነት ያወጣሃል። ዮሐ.8፥32። ቃሉ መርምረኝ ቻል ብለህ አትለፈኝ ይልሃል። መርምረህ ተረዳና ከጥፋት ዳን።



የጀርመን ብሔራዊ የስላሴ ምስል በ19ኛ ው ክፍለ ዘመን

http://www.sayadi-al-nas.com